# የብአዴን 30ኛ ዓመት ክብረ በዓል በለንደን በድምቀት ተከበረ

የብሔረ አማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብአዴን/ የተመሰረተበት 30ኛ ዓመት በለንደን የኢትዮጵያ ኤምባሲ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የድርጅቱ ደጋፊዎች በተገኙበት በድምቀት ተከበረ።

የያኔው ኢህዴን/ብአዴን ከሌሎች የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጐን በመቆም በከፈለው መስዋዕትነት አምባገነናዊው የደርግ መንግስት ተገርስሶ በምትኩ አዲስ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባቱን የጠቀሱት የኤምባሲው ተወካይ አቶ ሀብቶም አብርሃ ዛሬ የሀገራችን ሕዝቦች በዕድገትና በሰላም ጐዳና በመረማመድ ላይ ናቸው ብለዋል።

ብአዴንና አጋር ድርጅቶች በጋራ ግንባራቸው በኢህአዴግ ጥላ ስር ተሰባስበው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦች በመፈቃቀድ በእኩልነትና በመተሳሰብ የሚኖሩባት የበለፀገች ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት በቀየሱት የልማትና የዲሞክራሲ ትልም አዲስ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ለተከታታይ ዓመታት የተመዘገበ ፈጣን ዕድገት ዕውን ማድረግ ችለዋል ሲሉ አቶ ሃብቶም ገልፀዋል።

ብአዴን የአማራ ክልል ሕዝብ የአካባቢውን ዕድገት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በባሕላዊ ዘርፍ ለማሳደግ ከፍ ያለ ርብርብ ከማድረግ በተጨማሪ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በመሆን ሰላማችንና ዘላቂ ልማታችን ተጠናክሮ እንዲቀጥል በቁርጠኝነት እንደሚዋጋ ጠቅሰው ለዚህ ዓላማው መሳካት ሁሉም የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መላው ሕብረተሰብ ከጐኑ እንደሚሰለፍ ተወካዩ አረጋግጠዋል።

በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት በተተለመው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊነት የሕዝቡን ሕይወት ይበልጥ ለማሻሻል በሚደረገው ርብርብ ብአዴን፣ አባላቱና ደጋፊዎቹ የድርሻቸውን እንደሚወጡም ተወካዩ ያላቸውን ዕኑ ዕምነት ገልፀዋል።

በለንደን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የኮሚኒቲ ዘርፍ ኃላፊና የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ተስፋዬ ይታይህ በበኩላቸው ኢህዴን/ብአዴን የቆመለት ዓላማ ሕዝባዊነት በአማራ ክልል በሁሉም ዘርፎች በተለይም በጤና፣ በትምህርት በመሠረተ ልማት ወ.ዘ.ተ. በታዩ ለውጦች በሚገባ ተንፀባርቋል ብለዋል።

ዛሬ በክልሉ የታየው ከፍተኛ የትምህርት የጤና ሽፋን ዕድገት፣ የኤሌክትሪክና የቴሌኮሙኒኬሽን እንዲሁም የሌሎች መሠረተ ልማቶች ግንባታ ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የገለፁት አቶ ተስፋዬ ብአዴን/ኢህዴን የክልሉን ሕዝብ መብትና ጥቅም በማስከበር ከሌሎች ወንድም ብሔርና ብሔረሰቦች ጋር በእኩልነት በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በመሳተፍ የበለፀገች ኢትዮጵያን ይገነባል ብለዋል።

አቶ ተስፋዬ የኢህዴን/ብአዴን አመሠራረትንና ያለፈባቸውን የትግል ሂደቶች የሚያሳይ ገለፃ ሰጥተዋል።

በዕለቱ በእንግሊዝ ነዋሪ የሆኑ የኢትዮጵያ ሶማሌ ኮሚኒቲ የሰላምና የልማት ፎረም ተወካይ የሆኑት አቶ ኑር ሁሴን በዕለቱ ባሰሙት የአጋርነት መግለጫ የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብአዴን/ ደርግን ለመጣል በተደረገው ትግል እንዲሁም ከዚያ ወዲህ በማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ልማት እንዲሁም በዴሞክራሲ ግንባታ በኢሕአዴግ አባል ድርጅቱነቱ ያበረከተው አስተዋጽኦ የጎላ ነው ብለዋል።

አያይዘውም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አዲሱን የዕድገት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የዜግነት ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

በዕለቱ በለንደን የሚገኘው የገና የኪነት ቡድን ባሕላዊ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎችን አቅርቧልቃ የቡና ማፍላት ሥነ-ሥርዓትም ተካሂዷል፣

ቀደም ሲል በዓሉን በማስመልከት የተዘጋጀው ድፎ ዳቦ የተቆረሰ ሲሆን የብአዴንን 30ኛ ዓመት ምሥረታን የሚያበስረው ሻማም በዕለቱ የክብር እንግዶች ተለኩሷል።